# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም:-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## <u>ዜና ዘገባ</u>

**ሚያዚያ 22 ቀን 2003 ዓ.ም.**

**ወያኔ ምሁራኖችን እያሳደደ በውጭ ምንዛሪ የውጭ ሀገር ዜጋ መቅጠሩ ቅሬታ ፈጠረ፤**

**የኦነግ አባል ናቸው ተብለው የታሰሩት በአስቸኳዋይ ስም ዝርዝራቸው ይገለፅልኝ ሲል መለስ ዜናዊ ትዕዛዝ ሰጠ፤**

**ዛሬ ነጋዴዎች በምሳ ግብዣ ስም ገንዘብ በግዴታ እንዲያዋጡ ተደረገ፤**

የወያኔ ቡድን ሀገሪቱ በችግር እና በርሀብ እየታመሰች ባለበት በዚህ ግዜ የሀገሪቱን ምሁራኖች እያባረረ በውድ ዋጋ ከውጭ ሀገር መምህራኖችን እየቀጠረ ማስመጣቱ መምህራኖችን ማስቆጣቱ ታወቀ::

በተለያዩ ዩኒቨርስቲ ውስጥ በመምህርነት እያገለገሉ ያሉትን ምሁራኖች የደመወዝ እድገት ሳይሰጥ ባሉበት እንዲረግጡ እያደረገ በሌላ በኩል ደግሞ ሀገሪቱ መክፈል ከምትችለው አቅም በላይ በውጭ ሀገር ምንዛሬ ከተለያዩ ሀገራት መምህራኖችን እያስመጣ መሆኑ ግራ የሚያጋባ ነው ተብሎዋል::

ሰሞኑንም ለረጅም ዓመታት የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት ነበረውን ፕሮፌሰር ኃይሌ ምትኬ አንስቶ በምትኩ ከውጭ ሀገር በውድ ክፍያ የጀርመን ዜግነት ያለው ሰው ማስመጣቱ በዩኒቨርስቲው መምህራኖች ዘንድ እያነጋገረ መሆኑ ታውቆዋል::

የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት የነበረው ፕሮፌሰር ምትኩ ኃይሌ ከዚህ ቀደም በመለስ ዜናዊ ጭምር ሲሞገስና ሲወደስ የነበረ ሲሆን አሁን ለውጥ አላመጣም በሚል ከቦታው ድንገት እንዲነሳ ተደርጎ የጀርመን ዜግነት ያለው ሰው ማስቀመጡ እያነጋገረ መሆኑ ታውቆዋል::

ዶክተር ጀሀሚን ሀርዚንግ የተባለው ጀርመናዊ ዜጋ በያዝነው ወር መጀመሪያ ላይ ስራ እንዲጀምር ሲደረግ መኖሪያ ቤትንና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን ሳይጨምር በወር ከ160 ሺህ ብር በላይ እየተከፈለው የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት እንዲሆን መመደቡ ብዙ የዩኒቨርስቲው መምህራኖችን ቅሬታ አስነስቶዋል::

በአሁኑ ሰዓት በርካታ ምሁራኖች በፖለቲካ አመለካከታቸው ብቻ እየተፈናቀሉና ከሀገር እንዲሰደዱ እየተደረገ ባለበት በዚህ ግዜ ሀገሪቱ መክፈል ከምትችለው በላይ በውጭ ምንዛሬ የውጭ ሀገር ዜጎችን ቀጥሮ ማስመጣቱ ብዙ ምሁራኖችን እያበሳጨ መሆኑም ታውቆዋል።

አንድ የዩኒቨርስቲ መምህር በወር ከ5 ሺህ ብር በላይ ሳይከፈለው አልፎ ተርፎ ለወያኔ ባለው አመለካከት እየተባለ በሚፈናቀልበት በዚህ ግዜ ለአንድ ግለሰብ ይሄን ያህል ከፍተኛ መጠን ያለው ብር መክፈሉ አላስፈላጊ ከመሆኑም በተጨማሪ የሀገርን ሀብት ማባከንና ዜጋን መናቅ ነው ሲሉም ምሁራኖች የወያኔ አሰራርን ይተቻሉ።

በመላ ሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ምሁራኖችን ወያኔ የተለያዩ ሰበቦች እየለጠፈባቸው ወደ እስር ቤት እያጎራቸው ከመሆኑም በላይ በምስጢር በደህንነት ሰዎች እያፈነ የት እንዳሉ የማይታወቁ በርካታ ከመሆናቸውም በተጨማሪ የወያኔን አረመኔ ድርጊት በመፍራት እጅግ ቁጥራቸው የበዙት ሀገራቸውንና ህዝባቸውን ጥለው እየተሰደዱ የሰው ሀገር አገልጋይ ሆነው እንደሚገኙ ይታወቃል።

ዛሬ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን ጨምሮ በሌሎችም ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ባሉ መምህራን ሳይቀር የጎሳ ፖለተካው ሰፍቶ .....እስከ መንደር ደረጃ ድረስ ዝቅ ብሎ ወርዶ..... ሀገራዊ ሳይሆን መንደራዊ...... ኢትዮጵያዊ ሳይሆን ብሔር መለያ ሆኖ ቡድንተኝነት እንዲሰፍን እየተደረገ በመሆኑ ተማሪዎች አንድ አቋም እንዳይይዙ እየተደረገ ይገኛል።

መምህራኖቹን ጭምር በብሔርና በጎጥ እየከፋፈሉ አንዱ አንዱን እንዲጠብቅ እየተደረገ የትምህርት አሰጣጡ ተበላሽቶና ወድቆ ከትምህርት ይልቅ ፖለቲካ ቅድሚያ ተሰጥቶት ትውልድ በእውቀት እየተጎዳ ያለበት ግዜ መድረሱንም ምሁራኖች በቁጭት ይገልፃሉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ግራ የገባው የወያኔ ቡድን ሰሞኑን ለየእስር ቤት አዛዦች አስቸኳዋይ ትዕዛዝ በምሥጢር ማስተላለፉን ከፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ሾልኮ የደረሰን ዘገባ አጋለጠ።

የወያኔው ቡድን መሪ መለስ ዜናዊ የሻዕቢያ ተላላኪ ናቸው እያለ ሲያወግዛቸውና ሲያብጠለጥላቸው የነበሩትንና በየእስር ቤቶቹ ውስጥ ያሉትን የኦነግ አባሎች የስም ዝርዝራቸው ተለቅሞ እንዲሰጠው በሰጠው ትዕዘዝ መሰረት ሰሞኑን ተግባራዊ መደረጉ ተገለፀ።

የኦነግ አባል ናቸው.... የሸዕቢያን ተልዕኮ ፈፃሚ ናቸው.....በማለት ከየቤታቸው....ከመስሪያ ቤታቸው..... ከንግድ ቦታዎቻቸው እንዲያም ሲል ከየጎዳናው ላይ አፍሶ ያጎራቸውን ዜጎች በምስጢር ከያሉበት እስር ቤት ተመዝግቦ ስም ዝርዝራቸው እንዲላክለት ትዕዛዝ ማስተላለፉን የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል።

ከከተማና ከገጠር እየታፈሱ በዝዋይ ፣በድሬዳዋ፣ በቃሊቲና በሌሎችም እስር ቤቶች ውስጥ ታስረው ያሉት የኦነግ አባሎች በሙሉ በአስቸኳዋይ ስም ዝረዝራቸው ተለቅሞ ይምጣልኝ ሲል በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር በዶክተር ሽፈራው ተክለማርያም ፊርማ የተላከላቸው የእስር ቤቶቹ

አለቆች በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሰረት ተግባራዊ መደረጉን የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ምንጮች ገልፀዋል፡፡

በቅርቡ ከየጎዳናው ላይ እየታፈሱ ወደ ማዕከላዊ እስር ቤት የታጎሩትና በሌሎች የምርመራ ማዕከላት የገቡትን የሚያጠቃልል አለመሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ በአሁኑ ሰዓት በግዜ ቀጠሮ በፍርድ ቤት የሚመላለሱና በፍርድ ላይ የሚገኙትን ብቻ የሚመለከት ትእዛዝ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

መለስ ዜናዊ አባይን እገነባለሁ ባለ ማግስት ተመልሶ ሻዕቢያን አጠፋለሁ እያለ እየፎከረ ባለበት በዚህ ግዜ ከየእስር ቤቶቹ ውስጥ ያሉት የኦነግ አባሎች ስም ዝርዝራቸው ተለቅሞ ይምጣልኝ ብሎ በሽፈራው በኩል ትዕዘዝ መስጠቱ ምን አዲስ ነገር ሊከሰት ይሆን ሲሉም ምንጮቹ ይጠቃይሉ፡፡

አንዳንድ የቃሊቲ እስር ቤት ፖሊሶች እንደሚሉት ከሆነ የወያኔ ቡድን ከዚህ ቀደም የሱማሌ ክልል ህዝብን ድጋፍ ለማግኘት ሲል ጥቂት ውጭ ሀገር የነበሩ የኦብነግ አመራሮች ጋር ተስማማሁ በማለት በይፋ የስምምነት ፊርማ ካደረገ በጥቂት ቀናት ውስጥ አብዱልመጅድ ሁሴን ላይ የመግደል ሙከራ አድርገዋል የተባሉትን የግንባሩ አባሎች እና የሞት ፍርድ የተፈረደባቸውን ጭምር ከየእስር ቤቱ የፈታ ሲሆን አሁንም በተመሳሳይ የኦነግ አባሎችን ሊፈታ ይሆናል ሲሉ ግምታቸውን ይሰነዝራሉ፡፡

አንዳንድ የፖለቲካ አዋቂዎች እንደሚሉት ከሆነ ደግሞ ወያኔ ጊዜያዊ የፖለቲካ መጠቀሚያ ለማድረግና ከህዝቡ ድጋፍ ለማግኘት ሲል አልፎ ተርፎ በውጭ ሀገር የሚገኙ የኦሮሞ ተወላጆችን ለማታለል እና ለማግባባት የሚወስደው እርምጃ ሊሆን ይችላል የሚሉ ሲሆን ሌሎች ደግሞ በቅርቡ መለስ ዜናዊ ከሻዕቢያ ጋር ጦርነት እገጥማለሁ ባለው መሰረት የተወሰነ ስልጠናና ተሀድሶ ሰጥቶ ሊያዘምታቸው ይችላል ሰሉም አስተያየት ሲሰጡ ይደመጣሉ፡፡

በተለያዩ እስር ቤቶች ውስጥ እየተሰቃዩ ካሉት ዜጎች መሀከል ሀገሪቱ ብዙ ገንዘብ ወጪ አድርጋ ያስተማረቻቸው ዶክተሮች መሀንዲሶች እና በሌላም መስክ የተማሩ ምሁራኖች የሚገኙ ሲሆን በተለይ የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑት የምህንድስና ባለሙያዎች ከዛሬ አንድ ዓመት በፊት ከያሉበት ቦታ ተለቅመው ለእስር የተዳረጉ ሲሆን እስከ አሁን የት እንዳሉም እንደማይታወቅ ቤተሰቦቻቸው እያለቀሱ ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

ዛሬ በመላ ሀገሪቱ ውስጥ በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በየእስር ቤቱ ታጉረው የሚገኙ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የኦሮሞ እስረኞች መሆናቸውን አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱ ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

የአይናቸው ቀለም አላማረኝም..... የሻእቢያ ቅጥረኛ ናቸው .....እያለ ሲደነፋባቸውና ሲያብጠለጥላቸው አልፎ ተርፎ አሰቃቂ የግፍ እርምጃ ሲወስድባቸው የነበረው ወያኔ ላይ በውጭ ሀገር የሚኖሩ አትዮጵያውያን ተቃውሞ በማሰማታቸው እና በማውገዛቸው ሁኔታው እንዲረግብ ለማድረግ ሲል የሚወስደው እርምጃ ሊሆን ይቸላል የሚሉ ምሁራኖችም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም፡፡

በሌላ ዜና አባይ ግድብን እገነባለሁ ብሎ ለፖለቲካ መጠቀሚያነት እያዋለው ያለው ወያኔ ህዝቡን በግዳጅ ገንዘብ እንዲያዋጣ በማድረጉ ከፍተኛ ተቃውሞ እያጋጠመው መሆኑ ከተለያዩ ስፍራዎች የደረሰን ጥቆማ ገለፀ::

በአባይ ግድብ ፕሮጀክት ዙሪያ ከፍተኛ ቅስቀሳ እያደረገ ያለው  ወያኔ ለህዝብ እና ለሀገር አስቦ ሳይሆን የስልጣን እድሜውን ሊያራዝምበት አቅዶና ተዘጋጅቶ የነደፈው ስልት ነው በሚል የተቃዋሚ አመራሮች እየሞገቱ ሲሆን ህዝቡ በበኩሉ ለታቀደው እቅድ በግዳጅ እንድናዋጣ መደረጉ የሚያሳዝንና የወቅቱን ሁኔታ ያላገናዘበ ነው ሲሉ አምርረው እየተቃወሙ መሆኑ ታውቆዋል::

በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኙ የመንግስት  ሰራተኞች ከአምስት ወር በፊት የኦሮሞ ልማት ማህበርን ለመርዳት በሚል በግዳጅ የአንድ ወር ደመወዛቸውን በዓመት እንዲከፍሉ በመደረጉ አሁን ተጨማሪ ሌላ መዋጮ አናዋጣም በማለት ተቃውሞ ማሰማት በመጀመራቸው ለግዜው የአባይ መዋጮ ጥያቄ እንዲቀር የተደረገላቸው ሲሆን በቅርቡ ደግሞ አማራና ትግራይ ክልል የሚገኙ ነዋሪዎች የግድብ ስራውን ብንደግፍም ገንዘብ አምጡ የሚባለውን እንቃወማለን በማለት ሰፊ ተቃውሞ እያሰሙ መሆኑ ታውቆዋል::

ዜጎች በረሀብ እንደ ቅጠል እየረገፉ በኑሮ ውድነት እየተሰቃዩ በለበት በዚህ ግዜ ወቅቱን ያላገናዘበ ያውም በግዴታ መዋጮ አምጡ መባሉ የዜግነት ክብራችንን የሚገፍ አልፎ ተርፎ የመኖር ህልውናችን የሚያናጋ በመሆኑ የአዋጡ ጥያቄውን አንቀበልም በማለት ምሬትና ተቃውሞ እያቀረቡ ይገኛሉ::

የእለት ጉርስ መሸፈን አቅቶን እየተንከራተትን ባለበት በዚህ ግዜ ይባስ ብሎ በቅርቡ ርሀብ ተከስቶ ወትሮ የነበረው  የእህል ዋጋ እየናረ መምጣቱን እያወቁ ይህችም ኑሮ ሆና አዋጡ በሎ ግዴታ መጣሉ የሚያሳዝን ከመሆኑም በተጨማሪ የሚያሳፍር ማሰቢያ አዕምሮ ያልፈጠረባቸው ግለሰቦች የተጠራቀሙበት ቡድን መሆኑን ያሳየ ነው ሲሉ በምሬት እየገለፁ ይገኛሉ::

ሰሞኑን በአማራ ክልል በጎንደር ፤በደሴ ፤በወልዲያ ከተማ ውስጥ የየቀበሌውና የየዞኑ ካድሬዎች ቤት ለቤት እየዞሩ በግዳጅ ህዝቡ እንዲያዋጡ ቢጠይቁም አንድም ነዋሪ ሳይሰጣቸው ከመቅረቱም በተጨማሪ ይባስ ብሎ የምንበላው ሰላጣንና  ስለተቸገርን የእርዳታ እህል እንፈልጋለን በማለት በጥያቄ እያጣደፉ  ያባረሩዋቸው መሆኑ ታውቆዋል::

የትግራይ ክልል ህዝብም እንደ ሌሎቹ ሀገሪቱ ህዝቦች ሁሉ ችግርና መከራ ሲፈራረቅብን ዞር ብላችሁ ያላያችሁን ዛሬ የናንተ ፖለቲካ መጠገኛ እንዲሆናችሁ የአባይን ሰበብ አመጥታችሁ ብትወተውቱም ለራሳችን የእለት ጉርስ አጥተናል በማለት አሳፍሮ እንደመለሳቸው ከትግራይ የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

ቅድሚያ በርሀብ እያለቀ ያለውን ወገናችንን ህይወቱን መታደግ...... የኑሮ ውድነቱን ውጥረት ማርገብ.... የተቸገረውን መርዳት ሲገባቸው ድንገት የእነሱ ፖለቲካ ኪሳራ ገጥሞት ሽፋን ለማድረግ ሲያስቡ ችግረኛን ህዝብ መልሶ ማስጨነቅ አግባብ አይደለም ያለው የትግራይ ህዝብ ገንዘብ ስለሌለን አናዋጣም በማለት አሳፍሮ እንዳባረራቸው የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል::

ህዝቡ መዋጮውን አናዋጣም ያለው የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ውስጡን ቅስቀሳ እያደረጉ በመሆኑ ነው ያሉት የወያኔ ካድሬዎች ህዝቡ በግድ እንዲያዋጣ ለማድረግ የሚችሉበትን መንገድ እንደገና እንደ አዲስ ቀይሰው ይህን መዋጮ የማያዋጣ የተቃዋሚ ድርጅት አባል ነው እያሉ ታፔላ እየለጠፉ ሊያስፈራሩት መዘጋጀታቸውን የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል::

ህዝቡ ግን ያመጣችሁትን አምጡ .....ያላችሁትን በሉን ......የእለት ጉርስ የሌለን የሚቀመስ የሚላስ ያጣን ...... ልጆቻችንን መመገብ የተሳነን ሰዎች እንደገና ገንዘብ አምጡ ብላችሁ መጠየቃችሁ የሚሳፍር ነው ሲሉም መረር እና ከረር ያለ መላሽ እየሰጣቸው እንደሚገኝ ታውቆዋል::

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥም ሰሞኑን የተጀመረው የማስፈራሪያ ዘመቻን ተከትሎ በየቤቱ በተለይ የንግድ ቤቶች እየተዘዋወሩ በአንድ ቤት ዝቅተኛው አንድ ሺህ ብር እየሰበሰቡ ህዝቡን እያማረሩት መሆኑ ታውቆዋል::

ነጋዴውን ከገበያ ውጭ ለማድረግ ታስቦ እና ታቅዶ እየሰሩበት በመሆኑ ዛሬ አንድም ነጋዴ ከውጭ አስመጥቶ የሚያከፋፍለው ነገር በሌለበት በዚህ ወቅት በግዳጅ የቦንድ ግዢ እንዲፈጽምና በነጻ እንዲለግስ እየተደረገ መሆኑም ታውቆዋል::

በመርካቶ ውስጥ የሚገኙ ትልቅም ሆነ ትንሽ ሱቆች ሳይሉ በነፍስ ወከፍ አንድ አንድ ሺህ ብር በግዳጅ እየተቀበሉዋቸው ሲሆን ከዚህ ሌላ ደግሞ የትልልቅ ሱቅ ባለቤቶች ለብቻ ተመርጠው እሁድ የምሳ ግብዣ እንደተረገላቸው ከደረሳቸው የጥሪ ወረቀት ለማወቅ ችሎዋል::

የመግቢያ ዋጋው አንድ ሺህ ብር የሆነው ይሄው የግዳጅ ምሳ ግብዣ በግርማ ወ/ጊዮርጊስ እና በመለስ ዜናዊ ስም ጥሪ ተደርጎ የተሰጣቸው ሲሆን በዚሁ ግዜ ነጋዴው የእርዳታ እጁን እንዲዘረጋ ለማስገደድ ጭምር ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑ ታውቆዋል::

ያሽመደመዱትን ነጋዴ ጨርሶ ሊቀብሩት እየተራወጡ ያሉት እነ መለስ ዜናዊ ዛሬ እሁድ ሚያዚያ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ከቀኑ 5 ሰዓት ጀምሮ ታዋቂ ነጋዴዎች ሙስሊሙም ሆነ ክርስቲያኑ አንድ ላይ መለስ ዜናዊና ግርማ ወ/ጊዮርጊስ በተገኙበት የምሳ ግብዣ ተብሎ የገንዘብ ማሰባሰብ ሂደት እንደሚደረግ ታውቆዋል::

የመግቢያ ዋጋ ክፍያው አንድ ሺህ ብር የሆነች (ቪአይፒ) የምትል ካርድ እየተሸጠላቸው ያሉት ትላልቅ እና ገንዘብ አላቸው የተባሉት ነጋዴዎች እየተመረጡ በመኖሪያ ቤታቸው ድረስ የተሰጣቸው ሲሆን ከየመሀሉ ነጋዴውን ሊያስተባብሩ ይችላሉ የተባሉት ተመርጠው ደግሞ ቅስቀሳ እያደረጉ እንደሚገኙ ታውቆዋል::

በዚሁ በሚደረገው ምሳ ግብዣ ላይ እያንዳንዱ ነጋዴ ቃል የሚገባበት ፎርም ተዘጋጅቶ የሚታደላቸው ሲሆን በዚህ ወረቀት ላይ የሚያሰፍሩትን የብር መጠን በአንድ ወር ግዜ ውስጥ ማስገባት እንዳለባቸው ከግርጌ ላይ የሰፈረው ማስታወሻ ያሳያል:: በተደረገው በዚሁ የገንዘብ ዝርፊያ ፕሮግራም ላይ በመቶ ሚሊዮኖች ብር ይገኛል ተብሎ የተገመተ ሲሆን ውጤቱ የሚታወቀው ግን በሁዋላ ነው::

በ1997 ዓ.ም በተደረገ ሀገር አቀፍ ምርጫ ላይ ነጋዴው ለተቃዋሚዎች ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ ስታደርጉ የነበራችሁት በፍላጎታችሁ እራሳችሁ አስባችሁ ነበር ዛሬ ግን ሀገር አቀፍ ለሆነ ጉዳይ ላይ እራሳችሁ አስባችሁ ልትሰጡ ይቅርና ያሰቡትን ሁሉ እንዳይሰጡ እያከላከላችሁ በመሆኑ ወደፊት እንነጋገርበታለን እያሉ በየሰፈሩ እና በየቤቱ እየዞሩ የሚያድሉት ካድሬዎች እየስፈራሩ ሲሆን ይህ ዘመቻ ደግሞ ነጋዴው በፍራቻ ይሄን ያህል ብር ለግሻለሁ እንዲል ሆን ተብሎ የተወጠነ ሴራ መሆኑም ታውቆዋል፡፡